## የሞራል እኩልነት ጥያቄዎችና የአመለካከት ችግራቸው: ምን ያህሉ ከተግባር ለመራቅ የሚደረግ እራስን የመሸንገያ መሳሪያ ነው?

**ብርሃኑ ነጋ[1]**

### 1. መግቢያ:

ባለፉት ሁለት ሳምንታት ለጉዳይ ወደ ደቡብ አፍሪካ በሄድኩ ጊዜ አንድ ከኢትዮጵያ ለህክምና የመጣ ወዳጄን አግኝቼ ትንሽ ገብስ ገብሱን ከተጫወትን በሁዋላ ቀስ በቀስ ወደማይቀረው የኢትዮጵያ ፖለቲካ ወሬ ገባንና ብዙም ሳንቆይ አንድ በጣም ጠንካራ የሆነና በጊዜው ትንሽ ያስደነገጠኝ ነገር ተናገረ:: ሰውዬው ያለው «መለስ ዜናዊ፣ መሀመድ አላሙዲና እናንተ ሁላችሁም አንድ ናችሁ:: ሁላችሁም እራሳችሁ የምትፈልጉትን ነገር በህዝቡ ላይ ለመጫን ነው የምትፈልጉት:: ለህዝቡ ፍላጎት ደንታ የላችሁም::» ነበር ያለኝ:: ይህንን የሚለኝ እራሱን በፍፁም ከፍተኛ የሆነ የሞራል ገገር መሬት ላይ አስቀምጦ ስለነበር በችኮላ መልስ ከመስጠቴ በፊት የሚለው ነገር በደንብ እንዲገባኝ ፈለግሁና አረፍተ ነገሩን ትንሽ እንዲያብራራልኝ ጠየቅሁት:: መለስ የሚፈልገውን ለማግኘት (ስልጣን ላይ ለመቆየት) ይገላል፣ ያስራል፣ ይዋሻል፣ የህዝብ ንብረት እንደግል ኪሱ ይጠቀማል:: አላሙዲ የሚፈልገውን ለማግኘት (ገንዘብ ማካበት፣ በገንዘብ የሚገኝ ተሰሚነት...ወዘተ) ገንዘቡን ይጠቀማል:: ከሞላ ጎደል ይጠቅሙኛል ያላቸውን ሰዎች ይገዛል:: እናንተም ቃላትን ተጠቅማችሁ የምትፈልጉትን ነገር በህዝቡ ላይ ለመጫን ትሞክራላችሁ:: ጉልበት አትጠቀሙ ይሆናል፣ ገንዘብ የላችሁ ይሆናል፣ ግን ህዝቡ የሚፈልገውን ከማድረግ ይልቅ እናንተ የምታምኑበትን ነገር በህዝቡ ላይ ለመጫን ነው የምትፈልጉት አለኝ::

ይህንን አይነት ነገር ሲናገር ምን ያህል አስቦበት፣ ምን ያህል የእውነት መሰረት አለው ብሎ አስቦ እንደሆነ ለማወቅ ከዚያ በላይ ዘልቆ እንዲያብራራልኝ ያደረግሁት ሙከራ በፍፁም አልተሳካልኝም:: ይህ ወዳጄ በቅንጅት ውስጥ በተፈጠረው ሁኔታ በጣም የተበሳጨ፣ ኢህአዴግ አሁን በአገሪቱ ላይ እያደረገ ባለው ፍፁም ቅጥ ያጣ የትእቢት እርምጃ አንጀቱ ያረረ መሆኑ ከንዴቱ ያስታውቃል:: ምንም እንኩዋን አንተ ሳይል በጥቅሉ «ተቃዋሚዋችን» ቢሆንም «እናንተ» ብሎ የተናገረው፣ ነገሩ የተሰማኝ ውስጤ ድረስ ነበር:: በመጀመሪያ ይህ ሰው በተናገረው ነገር ከተሰማኝ ድንጋጤ ስነቃ ቀጥሎ የተሰማኝ ፍፁም የመዘግነንና የመቆሸሽ ስሜት ነበር:: እንዴት ከነኝህ ሰዎች ጋር ያደባልቀኛል? ይህን ይህን አጥፍታችሁዋል ቢለኝ ልሰማ እችላለሁ:: እንዴት የእኛን ድርጊትና የእነመለስን ድርጊት በአንድ ሞራል መመዘኛ ውስጥ ይከተዋል? እሱ ምን በማድረጉ ነው ከእኔ በላይ የሞራል ስብእና አለኝ ብሎ ያመነው? ይህ ሰው ምን አይነት የሞራል ሚዛን ነው ተሸክሞ የሚዞረው? በመጨረሻም የዚህን ሰው ስሜት የሚጋሩ ምን ያህል ኢትዮጵያውያን ይኖራሉ? የሚሉ የጥያቄ ውርጅብኞች ነበር በጭንቅላቴ ውስጥ የሚዞረው:: ከሄድኩበት የሀሳብ መንገድ ተመልሼ መልስ ለመስጠት ስዘጋጅ ግን አይ! እኔ ከአሁን በሁዋላ ፖለቲካ ማውራትም አልፈልግም:: መስማትም አልፈልግም:: ዝም ብለን በወዳጅነታችን ሌላ ሌላ

[1] ይህ ንግግር በቶሮንቶ፣ ካናዳ አፕሪል 19፣ 2008 ዓ.ም. የተደረገ ነው::

ጫወታ እንጫወት አለኝ:: ሰውየው በጣም የምወደው ወዳጄ ነው:: ቀድሞም ፖለቲካ ብዙ የሚወድ አይደለም:: በምርጫው ሰሞን በነበረው ግርግር ትንሽ ለመደበሪያነት ከመከታተል በስተቀር ሰውየው በአጠቃላይ የህይወትና በተለይ ደግሞ የህይማኖት ሰው ነው:: ነገሩ ትንሽም አንጀቴን ያሳረረው ሰውየው ቀድሞውንም የተናገረው የፖለቲካ ጉዳይ ሳይሆን የሞራል ትክክለኛነት ጉዳይ ነበር፤ምን ያህል ከፍተኛ የሞራል ሰው ነኝ ብሎ እንደሚመካ ስለማውቅም ነበር::

ነገሩን ትንሽ ሰከን ብዬ ሳስበው ግን ከዚያም በፊት የሰማሁዋቸው ብዙ ነገሮች በፖለቲካ ውይይታችን ውስጥ እንዲህ አይነት «የሞራል እኩልነት» አስተያየቶች በተደጋጋሚ እንደሚሰነዘሩና በቂ መልስ እንደማይሰጣቸው ተረዳሁ:: በዚህም ምክንያት ፖለቲካችን የጠራ መስመር ይዞ እንዳይሄድ የበለጠ ሲያደፈርሱት አያለሁ:: እንዲህ መሰል የሞራል እኩልነት ምሳሌዎች ልጠቃቅስ:: በቅንጅት መሀከል የተፈጠረውን ትርምስ በሚመለከት በተደጋጋሚ የሚሰማ (ደግሞ ከአላዋቂዎች ብቻ አይደለም) አንድ ነገር ነበር:: ለችግሩ ተጠያቂዎች ሁሉም ናቸው የሚል:: ሁሉም አንድ ናቸው፤ ሁለቱም ወገኖች ለስልጣን ብለው ነው የሚጣሉት:: እንዲያውም አንዳንዶቹ ለሚሰጡት የሞራል እኩልነት የሰው ስም ሊሰጡት ሲፈልጉ (በዚህም ራሳቸውን በጣም የተለዩ ስለሚያደርጋቸው) የእከሌና የእከሌ የስልጣን ጠብ ነው...ወዘተ ይሉና ብዙ ትንተና የሚፈልግን የተመሰቃቀለ ነገር በአንድ የሰነፍና የግብዝ ጅራፍ ገርፈው፤ በዚህም ለራሳቸው ከፍተኛውን የሞራል «ገገር መሬት» ሰጥተው ያልፉታል::

ከሰሞኑ እየሰማነው ያለነው ሌላ ተመሳሳይ «የሞራል እኩልነት» ምሳሌ ደግሞ የትግል ስልትን በሚመለከት በሰፊው የሚነሳው ነው:: አመፅን የሚጠራ ማናቸውም አይነት የትግል ስልት የሞራል ደካማነት ነው:: በጉልበት የሚበድልን ሀይል በጉልበት መመከት በሞራል ሚዛን ሲመዘን ከበዳዩ ጋር አንድ መሆን ነው:: እንዲያውም ደፈር ሲል «ያለመሰልጠን ምልክት ነው» የሚሉ ፍፁም ጭፍን አስተያየቶች እየተሰጡ ነው:: እዚህ ላይ አድማጩ ልብ እንዲል የምፈልገው እነኝህ አስተያየቶች በሁለቱም በኩል የተወሰዱ ተጨባጭ እርምጃዎች ላይ በመመስረት (ለምሳሌ አምባገነናዊ ስርአትን በመቃወም ጠመንጃ ያነሱ ሀይሎች እራሳቸው በሲቪል ሰዎች ላይ የሀይል እርምጃ በመውሰዳቸው) አይደለም:: ወይንም በአንድ ተጨባጭ ሁኔታ ጠመንጃ ከማንሳት በተሻለና ባነሰ ወጪ ለውጥ ለማምጣት ይቻላል ከሚል ስሌት አይደለም:: በነኝያ ላይ ተመስርተው የሚሰነዘሩ አስተያየቶች በጥቅሉ ሳይሆን በቀረበው ማስረጃ ትክክለኛነት፤ በቀረበው ትንተና ምክንያታዊነትና አሳማኝነት ስለሚመዘኑ መለኪያው የተለየ ነው የሚሆነው:: ለዚህ ውይይት የማተኩርበት ዝም ብሎ ጠመንጃ ማንሳት ለምንም አላማ ይሁን በምንም ሁኔታ ይነሳ በሞራል ሚዛን ሲለካ እኩል ስህተት ነው የሚለውን ቀኖናዊ አመለካከት ነው::

እንደነኝህ አይነት በደንብ ያልተመነዘሩ ልቅ አስተያየቶች መሰረታዊ የአመለካከት ግድፈት የሚያንፀባርቁ ሀሳቦች መሆናቸው ብቻ ሳይሆን አሁን ላለንበትና ወደፊትም ለሚገጥሙን የትግል ፈተናዎች ብዙ አይረዱም፤ አይናችንን ከኩዋሱ ላይ እንድናነሳ ያደርጉናል፤ መንገዳችንን ግልፅ ያልሆነ በአቡዋራ የተሸፈነ የመደናበር ጉዞ ያደርገዋል፤ በትግሉ ውስጥ በስፋት ሊሳተፉ የሚችሉ ሀይሎችን ተስፋ ያስቆርጣል፤ በዚህም ምክንያት ከዚህ አካሄድ የሚጠቀመው ሁላችንንም በአምባገነንነት ማቅ

ውስጥ የከተተንና የታሰርንበትን የነፃነት ማጣት ሰንሰለት ተባብረን እንዳንበጥስ ያለ የሌለ ሀይሉን ሁሉ የሚጠቀመውን የኢህአዴግን አገዛዝ ብቻ ነው፤ ብዬ ስለማምን የዚህን አመለካከት ድክመቶች በሚመለከት ያለኝን የግል አስተያየት ለዛሬ ውይይታችን መነሻ እንዲሆን መረጥኩት፡፡ በዚያ መነሻ ሀሳብ ላይ ተመስርቼ ደግሞ አሁን ያለንበትንና የሚጠብቀንን የትግል ሁኔታ በሚመለከት የምለው ጥቂት ይኖረኛል፡፡

እነኝህን ጥያቄዎች በሚመለከት ያሉኝን አስተያየቶች ከመሰንዘሬ በፊት ጋባዦቼን በማመስገን ልጀምር፡፡ እዚህ ካናዳ እንድመጣና ከኢትዮጵያውያን ጋር ውይይት እንዳረግ የቅንጅት ድጋፍ ሰጪ ማህበር ሲጋብዘኝ ብዙ ጊዜ ሆኖአል፡፡ በተለያየ ምክንያት ሳይሳካ ቀረ እንጂ፡፡ የቅንጅት የልዑካን ቡድን ስራውን ጨርሶ ከተበተነ ጀምሮ የማቀርበው ማናቸውም አስተያየት የግሌ እንደሆነና ማንንም እንደማልወክል በግልፅ በመናገር ነው የምጀምረው፡፡ ዛሬም እንደዚሁ፡፡ ሆኖም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለይ «የዴሞክራሲያዊ ትግሉን ለድል ለማብቃት ምን አይነት እስትራቴጂ መከተል አለብን?»በሚለው ጥያቄ ላይ ያሉኝ አመለካከቶች «የቅንጅት ታሪካዊ ማንነት በቸኛ ባላደራዎች» ነን ብለው ከሚያምኑ ሀይሎች ጋር ለየት እያለ ስለመጣና፤ እነሱም ትንሽ ሲጨነቁ ስላየሁ፤ እኔ ራሴ በእንዲህ አይነት መድረኮች ላለመቅረብ ስከላከል ቆይቻለሁ፡፡ ዛሬም በብዙ እጅ መጠምዘዝ ነው የመጣሁት፡፡ እንድመጣም ያስወሰነኝ በድርጅቱ ውስጥ ያሉት አባላት እራሳቸውን «ዴሞክራሲያዊ የብዙሀን ድርጅት ነን» በማለት በወሬ ሳይወሰኑ ይህንንው በተግባር ለማሳየት የተለያዩ አመለካከቶችን ለመስማት ዝግጁ ነን ብለው፤ ይህ ልዩነት እንዳለ አውቀው ስለጋበዙኝ ይህንን የዴሞክራሲ መንፈስ በማክበር ነው፡፡ ይህ መንፈስ በሁሉም ቦታ እየተጠናከረ እንደሚመጣ ተስፋ አለኝ፡፡ ለማንኛውም አክብራችሁ ስለጋበዛችሁኝ እግዚአብሄር ያክብርልኝ፡፡

## 2. የቀረቡት የሞራል እኩልነቶች የአመለካከት ግድፈቶች፡፡

ከላይ በመግቢያዬ ላይ ያነሳሁዋቸውን ምሳሌዎች አንድ በአንድ በማንሳት ለምን የተሳሳቱ እንደሚመስለኝ በአጭሩ በማቀረብ ልጀምር፡፡ መለስ አላሙዲና እኛ አንድ ናችሁ የሚለውን የሞራል እኩልነት ያቀረበው ሰው ለእንዲህ አይነት ጠቅላላ ንግግር (sweeping statement) በምክንያትነት ያቀረበው ሁላችሁም የራሳችሁን ፍላጎት ነው የምትከተሉት የሚለውን መመዘኛ ነው፡፡ ሁላችንም የራሳችንን ፍላጎት ነው የምንከተለው የሚለው አነጋገር ትክክል እንኳዋን ቢሆን ከዚያ ተነስቶ በቀጥታ ሁላችሁም አንድ ናችሁ ወደሚል መደምደሚያ አያደርስም፡፡ በመጀመሪያ የራስ ፍላጎት የሚባለው ነገር ምን እንደሆነ መገለፅ አለበት፡፡ የመለስ ፍላጎት ስልጣን ቢሆን፤ የአላሙዲ ፍላጎት ገንዘብ ቢሆን፤ የእኛ ፍላጎት ነፃነት ቢሆን መሰረታዊ በሆነው በምንፈልገው ነገር እንለያያለን ማለት ነው፡፡ ያንን ፍላጎታችንን ምን እርምጃ በመውሰድ ለማግኘት መፈለጋችንም በጣም ሊለያየን ይችላል፡፡ መለስ የሌላውን መብት በመርገጥ፤ ንፁሀንን በመግደል..ወዘተ፤ አላሙዲም ሀሊና የሌላቸው ሰዎችን እንደሸቀጥ እየገዛ ከሆነ ፍላጎቱን የሚያሳከውና እኛ ደግሞ ህዝብ ያለፍርሀት በሚመርጠውና ሰብአዊ መብታችንን በሚያከብር መንገስት

በመተዳደር ነው ነፃነታችንን የምናገኘው ብንል «የግል ፍላጎት አለን» ስለተባለ ብቻ አንድ የሞራል እኩልነት ላይ አያስቀምጠንም። የግል ፍላጎት የሚለው በራሱ በሁሉም ሰው ላይ በአንድ መልኩ ወይም በሌላ ስላለ ሰዎችን በሙሉ በሞራል ሚዛን እኩል አያደርጋቸውም። ሰው ሁሉ ሀብታም መሆን ይፈልጋል። ስለዚህ ገድሎ ሀብታም የሆነም፣ሰርቆና አጭበርብሮ ሀብታም የሆነም፣ ለምኖ ሀብታም የሆነም፣ ጉቦ በልቶ የበለፀገም፣ ሰርቶና ላቡን አንጠፍጥፎ ሀብታም የሆነም አንድ ነው የሚል አይነት የሞራል መሰረቱ ቅጥ አንባሩ የጠፋ አነጋገር ነው የሚሆነው። የሰውየው ንግግር ግን ከዚያም ያለፈ የእውነታ ግድፈት አለበት። «የራሳችሁን እንጂ ህዝብ ለሚፈልገው ደንታ የላችሁም» የሚለው። የሰውየውን ንግግር እሱን በሚጠቅመው መልኩ ትንሽ ላጠናክረውና «እናንተም ስልጣን ነበር የምትፈልጉት» በሚል ልተካው። እኔ እስከማውቀውና በቅንጅት ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ በሙሉ ትግላችንን ያየሁት «ህዝብ የሚፈልገውን ይምረጥ» የሚል ሆኖ ነው። ስልጣኑን እንኳዋን ቢሆን የፈለግነው ህዝብ ከሚመርጠው ውጪ ስልጣን ላይ እንውጣ የሚል ነገር የለም። ታዲያ በእኩልነት ተወዳድሬ ህዝብ ከመረጠኝ ስልጣን ላይ መውጣት እፈልጋለሁ [2] ብሎ ለስልጣን የሚወዳደርና ከህዝብ ፍላጎት ውጭ በጉልበት፣ በማሰርና በመግደል ስልጣን ላይ ለመውጣት የሚፈልግ እንዴት በሞራል መለኪያ እኩል ይሆናል? ስለዚህ የእኛ ትግል የነበረው በቀጥታ ሰውየው የሚለው (ማለትም የህዝብ ፍላጎት) ይሁን ነው። ህዝብ የመረጠው ያስተዳድር፣ የህዝብ ፍላጎት (ምርጫ) ይከበር ነው ትግሉ። ታዲያ የቱጋ ነው እኛ የምንፈልገውን በግድ ለመጫን የሞከርነው? በምን የፍትሀዊነትና የሞራል መለኪያ ነው አንድ ሚዛን ላይ የምንቀመጠው?

የኢህአዴግ ደጋፊዎች በቅንጅት ውስጥ የተፈጠረውን ትርምስ በከፍተኛ ደረጃ ሲያናፍሱት በነበረበት ጊዜ በተደጋጋሚ ይሉት የነበረውም ይህንንው ነበር። ዋናው መልእክትም በሞራል መለኪያ ሁላችንም አንድ ነን፣ ለስልጣን ነው ትግላችን። ግን በብልጥነትና በጉልበት እንበልጣቸዋለን። አሸንፈናቸዋል። ስለዚህ የተሻልን ሰዎች ነን። የፖለቲካ ትግል ውስጥ የሞራል ጥያቄ አታግቡ ነው። ይህ ከተሳካላቸውና በበቂ ሰው ተቀባይነትን ካገኝ የትግሉን መሰረታዊ የሞራል መሰረት ናዱት ማለት ነው። ትግሉም ህዝብን የሚያስተባብርበት የላቀ የሞራል መሰረት ያጣና ይፍረከረካል። ስለዚህ የኢህአዴግ ፕሮፓጋንዲስቶች፣ ወይንም ኢህአዴግን ለመደገፋቸው እራሳቸውን ማሳመኛ ነገር ለሚፈልጉ ሆዳሞች ይህንን አይነት መሰረቱ የተናጋ ሎጂክ ቢያቀርቡ ባንደግፈውም ፍላጎታቸው ይገባናል።

ኢህአዴግን አጥብቆ ከሚጠላ ሰው አካባቢ የዚህ አይነቱ አስተሳሰብ ሲሰነዘር ስንሰማ ግን ከምር ልንወስደውና ምክንያቱን ለመረዳት መጣሩ ተገቢ ይመስለኛል። ከላይ በአጭሩ ለማሳየት እንደሞከርኩት የተባለው አባባል አሳማኝ የሆነ ምክንያታዊነት ኖሮት አይደለም። በውነቱ አንድ ጤነኛ ሰው በነገሩ ላይ በደንብ ተጨንቆ አስቦበት፣ አስቦም አምኖበት ይህንን ይናገራል ለማለት ያስቸግራል። እንዲያውም በአብዛኛው የዚህ አይነት አነጋገር የሚመስለው ጠንቀቅ ብሎ ማሰብን ከመፍራት ወይንም ከመሰልቸት

[2] ስልጣን ላይ ለመውጣት የተፈለገው በመጀመሪያ ለምንድን ነው የሚለውን (ገሚሱ ለመዝረፍ ሊሆን ይችላል፣ ገሚሱ ስልጣኑን በአግባብ ተጠቅሞ ማህበረሰቡን ለማበልፀግ ሊሆን ይችላል) በራሱ ከፍተኛ የሞራል ልዩነት የሚያስከትል ጥያቄ ለጊዜው ከግምት ሳናስገባ ማለት ነው።

የመጣ፤ የአስተሳሰብ ግዴለሽነት ወይም ስንፍና ነው የሚመስለው። ይህ ግን በጤናማነት ካየነው ነው። የበለጠ ከጎረጎርነው ከዚያም ከፍ ያለ የውስጥ ቀውስን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። ይህ የነፃነት ትግል ሁሉም ነፃነትን የሚወድ ሰው መታገል ያለበት ትግል መሆኑን የሚያውቁና በተለያየ ምክንያት እራሳቸውን ከዚህ ትግል አግልለው የቆዩ የራሳቸውን የሞራል ደካማነት ለመሸፈኛ በዚያ ትግል ውስጥ የገባውን በሙሉ ጥሩ የሞራል ግፊት የሌለው አድርጎ ለማቅረብ የሚሞክርም ሊሆን ይችላል። በተለይ የዚህ አይነቱ ንግግር «እናንተ ፖለቲካ ውስጥ የገባችሁ ሁሉ ቆሻሾች ናችሁ እኔ ግን እዚያ ውስጥ ያልገባሁት ንጡህ ስለሆንኩ ነው» ከሚል አይነት ቃና ጋር ሲቀርብ የዚያ አይነት የስነ አእምሮ ጠባሳ መሸፈኛ ለማድረግ ታስቦ ሊሆን ይችላል ብሎ መጠርጠሩ በጣም ከእውነት የራቀ አይመስለኝም።

በእኔ ግምት ግን ከሁሉም በላይ የዚህ አይነት አነጋገር የሚመጣው ከመበሳጨትና ትግሉን በጋጠሙት ችግሮች በመቆጨት፤ ኢህአዴግ በየእለቱ በሚወስዳቸው ወራዳና ነውረኛ ስራዎች በመብገን፤ ለብስጭቱ ማስተንፈሻ ተጠያቂ ለመፈለግ ነው። (በዚህ ሰሞን ኦባማ በኢኮኖሚ የተጎዱ የመሀል አሜሪካን ሰዎችን በሚመለከት በጭንቀት ጊዜ ወደ ምን አይነት አመለካከት እንደሚያዘነብሉ የሰጠው አስተያየት አይነት ማለት ነው) እንደ እውነቱ ከሆነ የዴሞክራሲ ትግሉ አካል ነን በሚሉ አንዳንድ አካላት በኩል የታየው የሞራል ዝቅጠት ምንም ለከት ማጣት በእርግጥ የሚዘገንን ነው። ይህ ግን ሁሉንም በአንድ የሞራል ቡሩሽ እንድንቀባ ሊያደርገን አይገባም። ምክንያቱም ትክክለኛ ካለመሆኑም ውጪ ተስፋ መቁረጥ የሚያመጣብን የአስተሳሰብ ብክለት መከራችንን ከማርዘሙ ውጪ ለችግራችን መፍትሄ ምንም አይረዳንም። የበለጠ የሚረዳን ጠንክር ብለን አስበን፤ እውነቱን ከውሸቱ ለይተን፤ ምርቱን ከግርዱ አጥርተን ትክክለኛውን መንገድ ይዘን በትግላችን መቀጠል ስንችል ብቻ ነው። **በሰነፍ አስተሳሰብና መንገድ ነፃነት አይገኝም።**

ሑለተኛው ምሳሌ ከላይኛው ምሳሌ ጋር የተመሳሰለ ስለሆነ ብዙ ጊዜ አላጠፋበትም። በአቶ ሀይሉና በሌሎቻችን መሀከል ከነበረው ልዩነት በመነሳት ችግሩ በሁለቱም በኩል የተፈጠረ ነው። ሁለቱም ለስልጣን ብለው ነው የተጣሉትና ድርጅቱን (ስለዚህም ትግሉን) ያዳከሙት በሚል ሁለቱንም ሀይሎች በእኩል የሞራል ሚዛን ላይ የማስቀመጥ ሙከራ ነው። ብዙ ጊዜ ይህን የሚሉት ሰዎች የትኛውን ድርጊት እንደሆነ በእኛ በኩል ጥፋት የሚሉትና ከእነ አቶ ሀይሉ ጋር በእኩልነት የሚያስቀምጡት በውነቱ ግልፅ አያደርጉትም። ምን አድርገን ቢሆን ነበር ከሞራል ተጠያቂነት ነፃ የምንሆነው? መቼም በአሁኑ ጊዜ በሚስጥር የተያዘ (የማይታወቅ) ነገር የለም። ሀቁ ለሁሉም ግልፅ ነው። አቶ ሀይሉ ከቅንጅት ሊቀመንበርነት ይውረድ የሚል ጥያቄ ተነስቶ አያውቅም። አሜሪካ እንዲመጣ የተላከው የልዑካን ቡድን የተመረጠው በሙሉ ድምፅ ነው፤ አቶ ሀይሉን ጨምሮ። ሁሉም ውሳኔዎች በሰፊ ውይይት፤ ቅንጅት ሁሌ እንደሚያደርገው ወይንም በሙሉ ድምፅ ወይንም በከፍተኛ አብላጫ ድምፅ ነው የተወሰነው። ከመጀመሪያ ከእስር ቤት ጀምሮ በብቸኝነት፤ ሌላውን አመራር ሳያማክር ውሳኔ ሲወስን የነበረው እሱ ነው፤ ይህም በሁዋላ በቅንጅት መሀከል ግጭት እንዳይፈጥር ተብሎ (እሱ እንዳይቀየም) ሁለቱም የቅንጅት የውጭ ቡድኖች እንዲፈርሱ የተወሰነው እሱን ለማባበልም ነበር። እሱም የተስማማበት ነው። ከዚህ ሁሉ በሁዋላም እኔ የምፈልገው ካልሆነ በቀር ለብቻዬ የፈለግሁትን አደርጋለሁ ብሎ፤ ለመካሪም፤ ላስታራቂም አልመች ብሎ የራሱን መንገድ የመረጠው እሱ ነው። ያንን

ችግር ከልዩነት ለማዳን በሌሎቻችን በኩል ሊደረግ የሚችለው አንድ ነገር ብቻ ነበር፡፡ በል አንተ የፈለግከውን አድርግ ብሎ የድርጅቱን ሀላፊነት በሙሉ ለሱ ትቶ፤ እሱ የሚወስነውን ውሳኔ ሁሉ «እሺ ጌታዬ» ብሎ መቀበል፡፡ ይህን ለምን አላደረጋችሁም ነው ክሱ? ከድርጅቱ ህግ፤ ከዴሞክራሲያዊነት መርሁ፤ በአመራርነት ከመረጡን አባላት ፍላጎት ሁሉ ውጪ እሱ ያለንን ብንቀበል ነበር በሞራል ትክክለኛ የምንባለው? እንዴት ነው የድርጅቱን መርሆች፤ ህጎች፤ አሰራሮች፤ ባጠቃላይም የድርጅቱን መሰረታዊ መንፈስ ጭምር የጣሰ ሰውና የለም እነኝህ መርሆች ይከበሩ፤ በህጋችን እንተዳደር፤ ዴሞክራሲያዊነትን እናክብር ያለ ሀይል ሁለቱም በአንድነት እኩል «የሞራል» ጥፋተኛ ናቸው የሚባለው? በሰላም ከተቀመጥክበት አንተ በማታውቀው ምክንያት አንድ ሰው መጥቶ ቢደበድብህና እራስህን ለመከላከል አንተም አንድ ሁለት ቡጢ ብትሰነዝር፤ አንተም በመጣላትህ ጥፋተኛ ነህ ብትባል ይዋጥልሀል? የዚህ አይነት **«ፍትህና እውነት የሌለበት» የሞራል መለኪያ በእውነት ሞራላዊ ነው?** በድርጅት ውስጥ በሚደረጉ ውይይቶችና ክርክሮች ልዩነቶች ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡ እንዲህ አይነት ልዩነቶችን ለማጥበብና በተቻለ መጠን ሁሉንም አቅፎ ለመሄድ ሙከራ ይደረጋል፡፡ ይህ ካልተቻለ በሚል የተፃፈ የድርጅት ሕገ ደንብ፤ ወይንም አንዳንድ ጊዜ በልምድ የተገኘ ሁሉም አባላት የሚያከብሩት አሰራር (organizational tradition) ይኖራል፡፡ ይህንን ግን ሁሉም ማክበር አለበት፡፡ ይህ ሕግ ለጥቂት ሰዎች የማይሰራ ከሆነ ድርጅቱ እንደ ድርጅት ሊቀጥል ይሳነዋል፡፡ አንድ ግለሰብ ወይንም ጥቂት ሰዎች ድርጅቱ በሚከተለው መስመር ወይንም ሊወስድ ባሰበው እርምጃ የማይስማሙ ከሆነና ይህንን ውሳኔ በውይይት ማስቀየር ካልቻሉ ያላቸው ምርጫ ወይንም የድርጅቱን ሕግ በተግባር እያከበሩ በድርጅቱ ውስጥ በሚካሄደው ውይይት በመካፈል የብዙሀኑን ሀሳብ ለማስቀየር (በዚህም የድርጅቱን አቋዋም ለማስለወጥ) መጣር፤ ወይንም በፍፁም ይህ ድርጅት መስመሩን ሰቱዋል፤ አብሬው ልጉዋዝ አልችልም ብለው ሲወስኑ ድርጅቱን መልቀቅ አዲሱን እምነታቸውን የሚያንፀባርቅ ሌላ ድርጅት መፍጠር ነው፡፡ በመስመራቸው ትክክለኛነት የሚተማመኑ መሪዎች አዲሱን እምነታቸውን (ከድርጅቱ የሚለዩበትን) ለህዝብ አቅርበው በንፁህ ውይይት ህዝቡንም ሆነ የድርጅቱን አባሎች ወደ እኛ መስመር መመለስ እንችላለን የሚል ልበ ሙሉነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ይህ ከሌላቸው ቀድሞውንም ከድርጅቱ የተለዩበት አሳማኝ ምክንያት የላቸውም ማለት ነው፡፡ የለም እኔ ያልኩት ካለሆነ ለማንም እንዳይሆን ድርጅቱን እበጠብጠዋለሁ፤ «ድርጅቱ እኔ ነኝ» ብዬ የራሴን መንገድ በድርጅቱ ስም (ተቀባይነት ኖረውም አልኖረውም) ዝም ብዬ እገፋለሁ ብቻ ሳይሆን የድርጅቱም ንብረትም ሆነ ምልክት የኔ ነው ብዬ ድርቅ እላለሁ፤ ለድርጅቱም ሆነ ለትግሉ ቅንጣት ታክል ክብር የሌላቸው መሆኑን የማውቃቸውን የታወቁ ውሸታሞች ሰብስቤ ሁሉንም በስድብ አዋርዳለሁ (እንዲህ አይነት ሰዎች በሁዋላ እራስህን እንደሚያዋርዱህ በመዘንጋት) የሚል እራስንም፤ ድርጅትንም አልፎም ትግሉን የሚያዋርድ አሳፋሪ ስራ መስራት ለከት የሌለው ትዕቢት ብቻ ሳይሆን፤ በተለይ በዴሞክራሲያዊ ፖለቲካ እራስን የማጥፋት (suicidal) ያላዋቂ ወይም በጣም የተሸበረ ሰው አካሄድ ነው፡፡ **አቶ ሀይሉ ያደረገው ደግሞ ይህንን ነው፡፡** በሌላ በኩል ያለነው በጊዜው በተደጋጋሚ የነገርነውም ይህንንው ነው፡፡ የተላክንበትን ስራ በጋራ እንስራ፡፡ የማይስማማህ ልዩነት ካለ የሚመለከተውን አካል ሰብስበህ ለማስለወጥ ሞክር፡፡ አብረንህ በምክር ቤት የተሰየምነው ሰዎች እኩዮችህ ነን (በእድሜ ሳይሆን)፤ ልክ እንዳንተ የመረጠን አካል አለ፡፡ ዋናው ሀላፊነታችንም ለዚያ ለመረጠን አካል ነው፡፡ ልዩነቶች ካሉህ ለዚያ አካል ነው ማቅረብ

የምትችለው፣ ዝም ብለህ ሀሳብህን ልትጭንብን አትችልም (ልዩነትህ የሀሳብ ከሆነ ማለት ነው) ነው የተባለው። **ይህን ሳናደርግ ብንቀር ኖሮና እሱን ለማስደሰት ወይንም ከመርህ የወጣ ጊዜያዊ ስምምነት ላማግኘት ብለን «ያልከው ሁሉ ይሁንልህ» ብንል ኖሮ ነበር እውነትም አላማ የሌለን፣ እምነት የሌለን፣ ለስልጣን ብቻ የምንታገል ተራ ፖለቲከኞች እንሆን የነበረው። በሞራል መለኪያ የምንጠየቅ የነበረው ያኔ ነበር።**

ይህም እንደመጀመሪያው ምሳሌ በብስጭትና በመቆጨት የሚባል ሊሆን ይችላል። ነገር ግን መሰረታዊ የአስተሳሰብ ግድፈት ያለበት አነጋገር መሆኑ የሚያከራክር አይሆንም። ወደፊትም እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለማምጣት ከሆነ ትግሉ በስርአቱ እውነተኛ መገለጫዎች ላይ የሚኖሩ ልዩነቶችን አጥርቶ፣ በነሱም ላይ ግልፅ የሆነ መግባባት ተፈጥሮና ለእነኝህ መርሆዎች ሁሉም ለመገዛት ወስኖ፣ በነኝህ ህጎች ለመገዛት የማይፈልገውን ትቶ ካልተንቀሳቀሰ  በስተቀር «አብሮ መታገል ጥሩ ነው» በሚል መርህ አልቦ ስምምነቶች መቀጠል ዞሮ ዞሮ መውጫ የሌለው ቀድሞ የገባንበት የሞራል ጨለማ ውስጥ ነው የሚከተን።

ሶስተኛውና የመጨረሻው ምሳሌ በቅርብ የተነሳ ግን በጣም ጊዜያዊና አስፈላጊ ክርክር ውስጥ ይከተኛል። የትግል ስልትን በሚመለከት የተነሳው ክርክር ነው። በኢትዮጵያ የትግል ስልትን በሚመለከት በሁለት ቀጠና የሚከፈሉ መከራከሪያዎች ይቀርባሉ። አንደኛው በመርህ ደረጃ የሚነሳው ክርክር ነው። ሁለተኛው ግን ማንኛውም የስልት ጥያቄ በትክክል ሊመዘንበት በሚገባው የውጤታማነት መለኪያ ነው። ጥያቄው በጥቅሉ የአመፅ እንቅስቃሴ በምንም ሁኔታ ተቀባይነት ይኖረዋል ወይ? የሚለው ሆኖ በተለይ ግን አሁን ባለው በኢትዮጵያ ሁኔታ ዴሞክራሲያዊ ስርአትን ለማምጣት ከኢህአዴግ ጋር የሚደረገው የአመፅ ትግል ተቀባይነት አለው ወይ? የሚለው ነው። ባለፈው ጊዜ ሎስ አንጀለስ ከተማ ውስጥ ባደረግሁት ንግግር የዚህ አይነት የትግል ስልት ወይንም ማንኛውም አይነት የትግል ስልት በኢትዮጵያ ሁኔታ ውጤታማ ይሆናል አይሆንም የሚለውን ለመመለስ በመጀመሪያ መመለስ አለባቸው ብዬ ብዙ ጥያቄዎችን መደርደሬ ይታወሳል። በዚህ ንግግር ላይ እነሱን ጥያቄዎች ለመመለስ አልሞክርም። ሌላ ጊዜ እመጣበታለሁ። ዛሬ ከላይ እንደጠቀስኩት መመልከት የፈለግሁት በመርህ ደረጃ የተነሳውን ጥያቄ ብቻ ነው። በተለይም ማንኛውም አይነት የጉልበት ትግል ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም ከሚል የሞራል ከፍተኛ መሬት የሚነሳውንና በተለይም ደግሞ አመጽን የተወሰነን ግብ ለማሳካት የሚጠቀሙ በሙሉ (ጉልበት የተጠቀመ ሁሉ) በሞራል መለኪያ አንድ ናቸው የሚለውን ሀሳብ በአጭሩ ለመተቸት ነው።

የጉልበት እርምጃ ባጠቃላይ ጥሩ ነው፣ ወይንም የሞራል ተቀባይነት አለው የሚል ክርክር የሚያነሳ የለም። የሰው ልጅ ያሉትን ግለሰባዊም ሆነ ማህበረሰባዊ ችግሮች በሰላማዊ መንገድ፣ በውይይትና በብልሀት ለመፍታት የሚያስችለው የማሰብና የማሰላሰል ችሎታ ከፈጣሪው ተሰጥቶታል። የሰው ልጅ ከሌላው የሚለየውም ይህ የማመዛዘን ችሎታውና ብልህነቱ ነው። የሚያሳዝነው ሁኔታ ግን አብዛኛው የሰው ልጅ የእስከአሁን ታሪኩ ችግሮቹን በሀይልና በጉልበት ከመፍታት አሁንም ሙሉ ለሙሉ አለማቆሙ ነው። ለዚህ ግን ሁሉም የሰው ልጅ የሞራል ተጠያቂ አይደለም። በእያንዳንዱ ሁኔታ ለተፈጠረው ቀውስ ተጠያቂው ማን ነው ተብሎ ነው በሞራልም ሆነ በህግ የሚጠየቀው። ይህ ደግሞ

ሁሉንም የአለማችንን ክፍል ከሞላ ጎደል ይመለከታል፤ ምንም እንኩዋን በእኛ አካባቢ የበለጠ ገዝፎ ቢታይም:: ከዚህ የታሪክ ሁኔታ በመነሳት ከሀይል ጋር በተያያዘ የሚነሳው የሞራል ጥያቄ ሀይል መጠቀም በምንም ሁኔታ ተቀባይነት የለውም በሚል ጭፍን ቀኖና የሚመራ ሳይሆን በምን ሁኔታ ነው ሀይልን መጠቀም የሞራል ተቀባይነት የሚኖረው ወደሚል ጥያቄ የጠበበው::

በሁለተኛው የአለም ጦርነት የጀርመንን አጥፊ የመስፋፋት ህልም ለመቅጨት ሌሎቹ የህብረት ሀይሎች ጦርነቱ ውስጥ ለምን ገቡ? ለምን በሰላም ለመጨረስ አልሞከሩም የሚል የሞራል ደንታቢስነት ክስ ተመስርቶባቸው አያውቅም:: እንዲያውም በጊዜው የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት ቻምበርሊን ሂትለርን ለማባበል በሚል በወሰዳቸው የማዘናጊያ እርምጃዎችና በዚህም ምክንያት ጦርነቱን በጊዜ ባለመቀላቀላቸው ምክንያት ሂትለር በቀጠፈው ብዙ ንፁህን ዜጎች (በተለይም ይሁዲዎች) ምክንያት በሞራል ደካማነት ይከሰሳሉ እንጂ:: የናዚን ጦር በሁሉም መንገድ የወጉ ታጣቂ ሀይሎች በሞራል መስፈርት ከናዚዎች ጋር በምንም አይነት ሊመሳሰሉ አይችሉም:: በአገራችን ጣልያንን በዱር በገደሉ የተዋጉ አርበኞች በጠመንጃ ነካሽነት በሞራል ደካማነት ሲከሰሱ ሰምቼ አላውቅም:: የሞራልና የግብረገብነት አስተማሪ የነበሩት አቡነ ጴጥሮስ በግዜው እንደነበሩ አንዳንድ የሀይማኖት አባቶች አርበኞችን መሳሪያቸውን አስቀምጠው እንዲገቡ ተማፅኑ ቢባሉ እምቢ፤ ለአገራቸውና ለነፃነታቸው መዋደቃቸው በእግዚአብሄር ፊትም አያስጠይቅም ስለዚህም አላወግዝም በማለታቸው ነው ህይወታቸውን ያጡት:: መቼም እሳቸውን በሞራል ድህነት የሚጠይቃቸው ያለ አይመስለኝም:: ቱርኮች አርመንያውያንን ለመጨረስ በሞከሩበት ወቅት የነበረውን አነስተኛ የአርመንያውያን ትግል፤ ሳዳም ሁሴን ኩርዶችን ለማጥፋት በኬሚካል መሳሪያ ሲፈጅ ይህን ለማስቆም የተደረገን የኩርዶች ትግል፤ ወይም እዚሁ እኛው መንደር የሁቱ ብሄረተኛ ዘር አጥፊዎች ቱትሲዎችንና ለዘብተኛ ሁቱዎችን ለማጥፋት ሲንቀሳቀሱ እነሱን ለማስቆምና ለማሸነፍ የተደረገውን ትግልና ሌሎች የዚህ አይነት በገፍ የሚቆጠሩ ግፍን በመሳሪያ ለመከላከል የተደረጉ አመፆችን ለምን በቶሎና የሚቻለውን ሁሉ ጉልበት ተጠቅመው ጭፍጨፋውን አላስቆሙም ተብለው ይጠየቁ እንደሆን እንጂ፤በጥቅሉ መሳሪያ ስለያዙ ብቻ ከግፍ ፈፃሚዎች ጋር አብሮ በመደፍጠጥ የሞራል እኩልነት የሚሰጥ፤ የግፍ ችግርን አይቶ የማያውቅ ከሌላ ፕላኔት የመጣ ካልሆነ በስተቀር በዚችው በአበሰኛ አለማችን የኖረ ትንሽም ታሪክን ያነበበ ሰው ሊሆን አይችልም:: ስለዚህ ጥያቄው እንደዚህ በድፍኑ በሞራል መለኪያ ውስጥ ገብቶ ሊመዘን አይችልም::

ይህ የሞራል ጥያቄ ደግሞ በጥቅል አገራዊ የፖለቲካ ጥያቄዎች ላይ ብቻ ሳይሆን በእለት ተእለት ኑሮአችን ላይም የሚገጥመን ነው:: ምናልባት ብዙዎቻችሁ ተመሳሳይ ሁኔታ ሳይገጥማችሁ አይቀርም በሚልና የምናነሳውን የተወሳሰበ የሀሳብ ጥያቄን መሬት ለማስረገጥ በልጅነቴ የደረሰ አንድ ገጠመኝን በምሳሌነት ላቅርብ:: ልጅ ሆነን በክረምት ብይ እንጫወት ነበር:: ነብሱን የጠላ አንድ ለዛ ቢስ የሰፈር ወጠምሻ ጎረምሳ ሁል ጊዜ በግድ አብሬያችሁ ካልተጫወትኩ ይለናል:: እምቢ ካልነው ይደበድበናል:: ካጫወትነውና ከተበላም ያሸነፈውን ልጅ ደብድቦ ብዮቹን በሙሉ ይወስድበታል:: ሰላም የምናገኘው እሱ ከበላ ብቻ ነው:: ለረጅም ጊዜ ዱላ እየፈራን እየተሸነፍን መግባት ሆነ ስራችን:: ብይ መግዢያ ገንዘቡ ደግሞ እንደልብ የለንም:: በመጨረሻ እየፈራን እየቸርን ከሱ ጋር ላለመጫወት ወሰንን:: ግን የሚተወን

አልሆነም፡፡ ከቤት በወጣን ቁጥር አንድ በአንድ ይደበድበናል፡፡ እቤታችን ታስረን ከተቀመጥን ክረምቱ እንዲሁ ማለፉ ነው፡፡ በልጅነት ደግሞ ክረምቱን ሙሉ እቤት ውስጥ ታስሮ መቀመጥ ምን አይነት ቅጣት እንደሆነ ታውቃላችሁ፡፡ በመጨረሻ ተነጋገርንና በአንድ ላይ አብረን ለማግጠም ወስነን ተዘጋጅተን ሄደን ገጠምነው፡፡ ሁለተኛ አይለመደኝም እስከሚል ድረስ ተጋግዘን አሸነው፡፡ ይህንን ያዩ የሰፈር ሰዎች ለቤተሰቦቻችን ነግረው አንዳንዶቹ ተገረፉ፡፡ ሁሉም ይሉን የነበረው ግን ከእንዲህ አይነት አደገኛ ቦዘኔ ጋር እንዴት ትደባደባላችሁ? መፍትሄው ዱላ አይደለም፤ በዱላ እሱን አትችሉትም ነው፡፡ ስትደባደቡ እናንተም እንደሱ ዱረዬ ሆናችሁ ማለት ነው፡፡ እነሱ እሱ የሚያደርገንን ነገር በሙሉ ያውቁታል፡፡ ምንም ሌላ መፍትሄ አልሰጡንም፡፡ ዝም ብላችሁ ተውት፤ በዚህ አመሉ እግዚአብሄር ባለ ቀን ይፈርድበታል ነበረ የሚሉን የነበረው፡፡ ለእኛ ግን አንድ ሙሉ ክረምት በዚያ አይነት እስር ቤት ከመኖር በሱው መሳሪያ ገጥመን እድላችንን መሞከር ነበር የመረጥነው፡፡ ለችግሩ እልባትም አገኘንለት፡፡ ይህ በሞራል መለኪያ እኛንም «በጉልበተኝነት» እኩል ያደርገናል? ከዚያ የቀለለ መንገድ ቢኖርና እሱን አሌ ብለን ይህንን ብንመርጥ እሺ፡፡ እሱ ምርጫ ካሳጣንና ወይ መታገል ወይንም ነፃነት ማጣት ከሆነ ምርጫው፤ እናንተ እኛ ቦታ ላይ ብትሆኑ የትኛውን ነው የምትመርጡት?

ስለዚህም ነው በዚህ ጉዳይ ላይ ትርፋማ የሆነ ውይይት ሊካሄድ የሚችለው አመፅ ለምን? አመፅ እንዴት? አመፅ ከየትኛው አማራጭ ጋር ሲመዘን? ከሚሉ ጥያቄዎች ጋር በጥንቃቄ ተገናዝቦ በሞራል መለኪያ ትክክለኛ ውሳኔ ላይ መድረስ የሚቻለው፡፡ አለበለዚያ በጭፍኑ ከሄድንበት በመጥፎና በጥሩ ድርጊቶች መሀከል የሞራል እኩልነትን መፍጠር ብቻ ሳይሆን መጥፎ ድርጊትን (ግፍ) በሰላማዊ መንገድ የፈፀመን (ለምሳሌ በፍርድ ቤት አስፈርዶ) የበለጠ «ሞራላዊና የሰለጠነ»፤ ክፉ ድርጊትን (ግፍን) በአመፅ የተቋቋቁዋመን «ኢሞራላዊና ያልሰለጠነ» ወደሚል መያዝያ መጨበጫ የጠፋው የሞራል ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ እንወድቃለን፡፡ ማንም ህብረተሰብ የጋራ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ህይወቱን በሚመለከት በእውነትና በሀሰት፤ በትክክለኛና ትክክለኛ ባልሆነ ተግባር፤ በጨዋነትና በብልግና፤ በፍትሀዊነትና በግፈኝነት እና በመሳሰሉት መሰረታዊ የሞራል ጥያቄዎች ላይ በሁሉም እንኩዋን ባይሆን በአብዛኛዎቹ ላይ ካልተስማማ፤ ወይንም ሌላ ቢቀር እነኝህን ጥያቄዎች በሚመዝንበት ቀመር ላይ ስምምነት ከሌለው የሞራል መሰረት ያለው የሰለጠነ ኑሮ ሊኖር አይችልም፡፡

ለውይይታችን እንዲረዳ በእኔ እምነት አመፅ በሞራል መለኪያ ተቀባይነት ሊኖረው የሚችልባቸውንና የማይችልባቸውን ሁኔታዎች በአጭሩ ላቅርብና ወደ ኢትዮጵያችን ሁኔታ ልመለስ፡፡ በጉዳዩ ላይ በሰፊው የተመራመሩበት ሰዎች ከዚህም የጠለቀና የሰፋ ትንተና እንደሚሰጡበት አያጠያይቅም፡፡ ለዚህ አጭር ንግግር ያክል ግን መመዘኛዎችን ቢያንስ የሚከተሉትን ማካተት አለበት እላለሁ፡

1) **<u>የአመፁ ምክንያት</u>**: በዚህ ስሌት በግልፅ የታወቀ ግፍንና ጭቆናን ለማስቆም ወይንም ለመመከት የሚደረግ የአመፅ ትግል በሞራል ተቀባይነት ያለው፤ ነገር ግን ግፍን ለመፈፀም፤ የሰዎችን (የግለሰቦችንም ሆነ የቡድኖችን) መብት ለመግፈፍ የሚደረግ የጉልበት እርምጃ በሞራል ተቀባይነት የሌለው፤

2) **<u>የአመፁ አይነት:</u>** አመፁ የሚካሄደው ግፉን የሚፈፅሙትን ወይንም የሚያስፈፅሙትን ለይቶ፤ በጉዳዩ ላይ ምንም ተሳትፎ የሌላቸውን ንፁሀን ሰዎች በፍፁም በማይነካ መልኩ (በተለይ ሆን ተብሎ ወይንም ከአጠቃላይ እስትራቴጂ አንፃር ጠቀሜታ አለው ከሚል ስሌት) በጥንቃቄ የተደረገ ከሆነና እንዲህ አይነት ሁኔታ በአጋጣሚ እንኳዋን ቢፈጠር በግልፅ ለመፀፀትና ከተቻለም ተጎጂዎችን ለመካስ ፈቃደኛነት ካሳየ:: ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ግፍ ፈፃሚዎች በተባሉትም ላይ ቢሆን ከጥላቻ በመጣ የበቀል ስሜት ሆን ብሎ ለመጉዳት ሳይሆን ግፋቸውን ለማስቆም በሚያስችል ተመጣጣኝ ሀይል የተፈፀመ ከሆነ፤ ይህ አመፅ በሞራል ሚዛን ተቀባይነት ይኖረዋል:: በአንፃሩ ግፍ ያልፈፀሙ ንፁሀን ዜጎች ላይ የሚደረግ ምንም አይነት የሀይል እርምጃ (የአመፁ ምክንያት ተቀባይነት እንኳዋን ቢኖረው)፤ ወይንም ለብቀላ ብቻ በሚል፤ ሆን ብሎ ሰውን ለመጉዳት የሚደረግ ለከት የሌለው ጉልበት የሞራል ተቀባይነት የሌለው፤

3) **<u>አመፅና አማራጩ</u>**: ግፍና ጭቆናን ለማስቆም ከጉልበት የተሻለና በውነትም ውጤት ሊያመጣ የሚችል ሆኖም ውጤቱ በግለሰቡ/በማህበረሰቡ ላይ ብዙ ኪሳራን ከማድረሱ በፊት ሊገኝ ከተቻለ፤ ይህን የተሻለ አማራጭ ሆን ብሎ ምንም እድል ሳይሰጡ፤ ወይንም አማራጩ እንዳይሰራ ሆን ብሎ እንቅፋት በመሆን ወደ ሀይል እርምጃ ከተሄደ በሞራል መመዘኛ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም:: ከዚያ ውጭ ግን ለሰላማዊ አማራጭ በቂ እድል ሰጥቶ፤ በግፍ አድራጊው እምቢተኛ ነት ይህ አማራጭ በምንም አይነት እንዳይሰራ ከተደረገ፤ ግፍን የሚቃወመው ሐይልን በመጠቀሙ የሞራል ድክመት አለበት ሊባል አይችልም:: በመጨረሻም:

4) **<u>ውጤታማነት</u>**: ይህ የሞራል መለኪያ ብቻ ሳይሆን የተግባራዊነት መለኪያም ነው:: በሞራል ጥያቄው ላይ ብቻ ስናተኩር በዚህ መለኪያ መሰረት የአመፅ ትግል የሚፈለገውን ውጤት በምንም አይነት ሊያመጣ እንደማይችል እየታወቀ፤ ወይም ሲከፋ ውጤቱ ከታሰበው ውጪ በጣም መጥፎ ሊሆን እንደሚችል እየታወቀ፤ ወይም ደግሞ ውጤቱ ማህበረሰቡን አሁን ካለበትም መጥፎ ሁኔታ የባሰ የከፋ ሁኔታ ውስጥ ሊያስገባው እንደሚችል እየታወቀ፤ አመፅ ውስጥ መግባት የሞራል ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም::

የአመፅን የሞራል መሰረት በሚመለከት እነኝህ መስፈርቶች ከሞላ ጎደል ተቀባይነት አላቸው ብለን ከተስማማን:: ከላይ ያነሳናቸውን ጥያቄዎች ለመመለስ የሚያስችለን የትንተና መሳሪያ ስላለን ጥያቄዎቹን በቀጥታ መመልከት እንችላለን:: በእኔ እምነት በእነኝህ በአራቱም መስፈርቶች አመፅ የሞራል ተቀባይነት ሊኖረው ይገባል ባልኩዋቸው ድርጊቶች ጥላ ስር የሚወድቅ የአመፅ ትግል ተቀባይነት አለው:: የመጀመሪያዎቹን ሶስቱን መስፈርቶች በሚመለከት ብዙ የሚያከራክር ጉዳይ ሊኖር አይችልም:: ስለዚህ በሚያከራክረው በአራተኛው መስፈርት ልጀምር::

አራተኛው መስፈርት በጣም አከራካሪ ሊሆን የሚችል ግን የሞራል ሚዛን ስናስቀምጥ ከግምት ልናስገባው የሚገባው ነው:: አከራካሪ የሚያደርገውም ውጤቱ ወደፊት የሚመጣና የማይታወቅ ስለሆነ ውሳኔው በሚወሰንበት ጊዜ ከግምት በቀር በእርግጠኛነት ልንናገረው ባለመቻላችን ነው:: እዚህ ላይ የሚጠበቅብን የሞራል ሚዛን ብቻ ሳይሆን የወደፊት ውጤቱ ምን ሊሆን ይችላል በሚለው ላይ

መተማመን ነው፡፡ ይህ ደግሞ በፍፁም ቀላል አይደለም፡፡ የወደፊቱን በእርግጠኛነት ለማወቅ የሚያስችለን ምትሀታዊ እውቀት ቢኖረንማ ኖሮ እንዲህ አይነት ብዥታ ውስጥ አንወድቅም ነበር፡፡ ተስፋ የምናደርገው የወደፊቱን በሚመለከት እርግጠኛ እውቀት ስለሌለን አሳማኝ ነው በሚባል የአምክህኖታዊ ትንተና ላይ በመመስረት ለመተማመን መሞከር ነው፡፡ **በዋናነት ግን ለአሁን ማለት የምንችለው የወደፊቱን ማወቅ የምንችል ከሆነ የሞራል ጥያቄው ቀላል ይሆናል፡፡ ምንም ውጤት የማያመጣ ግን ብዙ ጥፋት ሊያደርስ የሚችል እንቅስቃሴ ውስጥ መግባት በሞራልም በተራ አምክህኖታዊነትም ተቀባይነት አይኖረውም፡፡** ዋናውን የተግባር ጥያቄ ማለትም ውጤት ያመጣል አያመጣም የሚለውን ግን ጉዳዩ ከሚመለከተው ከዚያ ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት መመርመር ያለበት ነው፡፡

ከላይ የተነሳሁበት በመርህ ደረጃ አመፅን በሚመለከት ለሚነሳ «የሞራል እኩልነት» ጥያቄ ግን በአብዛኛ ው የሚመለከተው በመጀመሪያው ሶስቱ መስፈርቶች ላይ ስለሆነ ይህ የሰጠሁት ትንተና ግልፅ ወደ ሆነ መደምደሚያ ነው የሚያደርሰኝ፡፡ ይኸውም በእኔ እምነት፡

**ግልፅ የሆነ ግፍንና በደልን ለማስቆምና ፍትህን ለማምጣት፤ በእልህና በጥላቻ ላይ ሳይመሰረቱና ግፍና በደሉን በሚፈፅመው አካል ላይ ብቻ ያነጣጠረ፤በተቻለ መጠን ጉዳዩ የማይመለከታቸው ንፁሀን ወገኖች እንዳይጎዱ ከፍተኛ ጥንቃቄ አድርጎ ፤ ከአመፅ ውጪ ያለን ሰላማዊ አማራጭ በቂ እድል ሰጥቶ ብቻ ሳይሆን ለወደፊቱም በሩን ከፍቶ የሚንቀሳቀስ የአመፅ ትግል በሞራል መለኪያ ሙሉ ተቀባይነት አለው፡፡**

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ባለው የፖለቲካ ሁኔታ የአመፅ ትግል ተገቢ ነው? አይደለም? ለሚለው ጥየቄ መልስ ዝም ብሎ በጥቅሉ «አመፅ ሁሉ አንድ ነው፤ የሞራል ተቀባይነት የለውም» ወይንም «ያልሰለጠነ» አካሄድ ነው የሚለውን መከራከሪያ በፍፁም መሰረት የለውም ብዬ የማልቀበለውም ለዚህ ነው፡፡ ይህ ግን እኔ ሎሰ አንጀለስ ንግግሬ ላይና በተለይም አንዳርጋቸው በቅርቡ በዝርዝር ባወጣው ፅሁፍ ላይ ያነሳቸውንና በተግባር ደረጃ የሚነሱ ጥያቄዎችን (ከላይ በአራተኛው ጥያቄ ላይ የተነሱትን) በሙሉ አይመልስም፡፡ እዚያ ውስጥ በዚህ ንግግር ላይ ልግባበት ብል አድማጩን ማሰልቸት ብቻ ነው ጥቅሙ፡፡  ከላይ እንዳልኩት በዚህ ጉዳይ ላይ እኔ እራሴ ያለኝን አቋዋምም ሆነ ይህ አቋዋም ከዚህ በፊት እንደ ግለሰብም ሆነ እንደ ቅንጅት አመራር አባል ይዤ ከነበረው አቋዋም ጋር ያለውን ተመሳሳይነትና ልዩነት በቅርብ ጊዜ በሰፊው እመጣበታለሁ፡፡ ለአሁኑ ግን ይህንን ውይይት ለማጠቃለል ያክል ተያያዥነት ባላቸው ሁለት ጥያቄዎች ላይ ያሉኝን አጭር አስተያየቶች አቅርቤ ላብቃ፡፡

### 3. የሞራል ጥያቄ የሚነሳው ክፉ ነገር በማድረግ ብቻ ወይንስ ክፉ ነገርን እያዩ ካለመቃወም?

ክፉትን መታገል እንደሚታሰበው ቀላል አይደለም፡፡ ብዙ እዳ አለው፡፡ የእዳው መጠንም እንደ ክፋቱ አይነት ሊገዝፍም ሊቀልም ይችላል፡፡ አስቀያሚ ክፉትና ግፍ መሆኑን እያወቁም እራስን ከመጋፈጥ ማግለል በጣም የተለመደ የአብዛኛው የሰው ልጆች እንቅስቃሴ ነው፡፡ ቢቻል ሌሎች ሰዎች እዳውን

ተሸክመውልን ከችግሩ እንዲያወጡን፤ ካልተቻለም ምንም ለማይሳነው አንድ አምላክ ችግሩን መተው በግለሰብ ደረጃ እዳው ያነሰ በጋራ ግን ለችግሩ ቀጥተኛ መፍትሄ የማይሰጥ የተለመደ አካሄድ ነው:: ግፈኞችም የሚሰሩት ክፉ ነገር ያዋጣናል ብለው የሚያምኑት ይህንን የብዙሀኑን ዝምታ ተማምነው ነው:: ከፍተኛ የሞራል መሰረትና ስለዚህም ጠንካራ ህሊና ያላቸው ሰዎች ክፋትን ፊት ለፊት ገጥመው (ማሸነፍ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ) ለማሸነፍ ይጥራሉ፤ ትንሽ የሚቆረቁር ህሊና ያላቸው ግን ክፋትን ለመጋፈጥ ወኔው ያነሳቸው ብዙ ሰዎች ምንም ላለማድረጋቸው እራሳቸውን የሚያሳምኑበት ምክንያቶች ይፈልጋሉ:: ምንም ህሊና የሌላቸው ደግሞ ክፋትን ተቀላቅለው ከሱ የሚገኘውን ጥቅም ለመቁዋደስ ላይ ታች ይላሉ::

በመግቢያዬ ላይ ያነሳሁዋቸው የሞራል እኩልነት ጥያቄዎች በብዛት የሚነሱት ከሁለት አካባቢዎች መሆኑን ለመጠቆም ሞክሬአለሁ:: የመጀመሪያው በተግባር ምንም ከማያደርጉ ግን ምንም ላለማድረጋቸው መከላከያ የሚፈልጉ ሰዎች እንዲህ አይነትን የሞራል እኩልነት በማንሳትና በተግባር የተሰለፉትን ጥላሸት በመቀባት እራሳቸውን ቢያንስ በሞራል ሚዛን ከሌላው በላይ ለማድረግ የሚሞክሩ ግብዞች ናቸው:: እንዲህ አይነት ሰዎች ግን በድርጊት ላይ የተሰማሩ ሰዎችን በሚጠይቁበትና በሚመዝኑበት አፋቸው እራሳቸውን በዚሁ መለኪያ ሊጠይቁ የሚገባቸው ነገር አለ:: ይኸውም የሞራል ጥያቄ የሚነሳው ክፉ ነገር በማድረግ ብቻ ነው ወይንስ ክፉ ነገርን እያዩ ካለመቃወም? ግፍ ሲፈፀም እያዩ ዝም ብሎ መቀመጥ (ወይንም ምንም የግል እርምጃ ላለመውሰዳቸው አስር ምክንያት መደርደር) ከሞራል ተጠያቂነት ነፃ ያወጣልን? ወይንስ ዝም ብሎ ራስን የመሸንገያ መንገድ ነው? ይህ በሞራል መለኪያ ዝም ብሎ የሚታለፍ አይደለም:: በአለማችን በሰፊው ለሚታየው ግፍ አንዱ ምክንያቱ የብዙው ሰው በግፍ ፊት ዝምታን መምረጡ ነው:: አንድ ለጊዜው ስሙን የማላስታውሰው ይህ ሁኔታ በጣም ግራ የገባው ፀሀፊ እንዳለው «በጣም የሚያስፈራው የጥቂቶች ጭካኔ አይደለም፤ በጭካኔ ፊት የብዙዎቹ ዝምታ እንጂ::»

በሚገርም ሁኔታ እንዲህ አይነት ሰዎች በግፍ ፊት ምንም ባለማድረጋቸው የራሳቸውን የሞራል ውድቀት ከማመንና ከዚያ ለመውጣት መውሰድ ያለባቸውን እርምጃ ከመውሰድ ይልቅ «እራሱ ሰርቆ ጤነኛውን ቀድሞ ሌባ እንደሚል የሌባ አይነ ደረቅ» ቢያንስ ትንሽም ቢሆን አስተዋፅኦ ለማድረግ የሚሞክሩትን ለማራከስ በመሞከር አያቆሙም:: በጣም የተራቀቀ እራስን የመሸንገያ ምክንያቶች ይደረድራሉ:: በብዛትና በተለምዶ የሚቀርቡት ሶስት መከራከሪያዎች ናቸው:: እነኝህ መከራከሪያዎች ለዘመናት ምንም አይነት በጎ ለውጥን ለመቃወም የተለያዩ የአድህሮት ሀይሎች እንዴት ሲጠቀሙባቸው እንደቆዩና ለምን የተሳሳቱ መከራከሪያዎች እንደሆኑ እውቁ የእድገት ተመራማሪና ሀያሲ አልበርት ሒርሽማን (በእኔ ግርድፍ ትርጉም) አላስፈላጊ ውጤት የማምጣት (perversity thesis)፤ የከንቱ ድካምና (futility thesis)፤ የጉዳት አምጪ (jeopardy thesis) በሚል ሶስት መላምቶች አቀናብሮ አቅርቦአቸዋል::[3]

[3] Albert O. Hirshman: "The Rhetoric of Reaction: Perversity, Futility, Jeopardy. Cambridge, Belknap Press, 1991. Here is how Hirshman presented the issue in his own words: "[The] three principal reactive-reactionary theses, which I call the *perversity thesis* or thesis of the perverse effect, the *futility thesis*, and the *jeopardy thesis*. According to the *perversity* thesis, any

ይህንን የመተንተኛ መሳሪያ አሁን እኛ ከምንወያይበት ጉዳይ ጋር በተመሳሰለ አንጥራ ያቀረበችው ግን እውቁዋ የሕግ ምሁርና ፀሀፊ ሰማንታ ፓወር ናት::[4]

ሰማንታ ፓወር የተለያዩ የአሜሪካ መንግስታት ባለፈው 100 አመት ውስጥ በአለማችን የተደረጉ የጅምላ ፍጅቶችን ለማስቆም ያለውን አቅም አልተጠቀመም በሚል አምርራ ትከሳለች:: በዚህም የአሜሪካ መንግስት ከፍተኛ የሆነ የሞራል ውድቀት አሳይቶአል ትላለች:: በዚህ በአንደኛው የአለም ጦርነት አካባቢ በአርመኖች ፍጅት ጀምሮ፤ በሁለተኛው የአለም ጦርነት የይሁዲዎች እልቀት፤ በ1970 ዎቹ በካምፑቺያ ህዝብ ላይ የፖልፖት መንግስት የፈፀመውን የጅምላ ፍጅት፤ በ1980ዎቹ የሳዳም ሁሴን መንግስት በአገሩ ውስጥ ባሉ ኩርዶች ላይ የፈፀመው የኬሚካል መሳሪያ ፍጅት፤ ቀጥሎም የሰርብ ብሄረተኞች በቦዝንያ ሙስሊሞች ላይ የፈፀሙትን እልቂትና በመጨረሻም በሩዋንዳ የሁቱ ብሄረተኞች በቱትሲዎች ላይ ያደረጉትን ዘግናኝ ጭፍጨፋ በዳሰሰው ግሩም መፅሀፍዋ በየጊዜው የነበሩት የአሜሪካ አስተዳደሮች የማስቆም ችሎታው እያላቸው ምንም እርምጃ ላለመውሰድ የሚሰጥዋቸው የነበረውን አሳፋሪ መከራከሪያዎች በሶስት ከፍላ እንዳቀረበችው: (የቡሽ አስተዳደር የኢትዮጵያ መንግስት በሰላማዊ ሰዎች ላይ ላደረገው ጭፍጨፋ ምንም እርምጃ ላለመውሰድ ካቀረበው ምክንያት ጋር አንድ ስለሆነ እንዳለ ላቅርበው):

1) እርምጃ መውሰድ (የኢኮኖሚ ማዕቀብም ሆነ ወታደራዊ ጣልቃ ገብነት) የበለጠ ልናድነው የፈለግነውን ህዝብ ነው የምንጎዳው:: እነኝህ መንግስቶች በእኛ እርምጃ ተበሳጭተው እንዲያውም በህዝቡ ላይ ጉዳት ያደርሳሉ:: የኢኮኖሚ ማእቀብ ድሀውን ነው የሚጎዳው...ወዘተ
2) ምንም እርምጃ ብንወስድ ምንም ውጤት አያመጣም:: የኢኮኖሚ ማእቀብ ብናደርግ አገሮቹ የሚፈልጉትን ነገር ከሌላ አገር ያገኙታል (በዛሬ ግዜ ከቻይና)፤ እንዲያውም ከነሱ ጋር ከመጣላት እርዳታውን እየሰጡ ቀስ እያሉ ማባበል ይሻላል...ወዘተ
3) በራሱ ህዝብ ላይ ግፍ የሚሰራ መንግስትን የሚቀጣ እርምጃ መውሰድ ሁኔታውን የበለጠ በጣም ያካርረውና እስከአሁንም የተገኙትን አወንታዊ ግኝቶች እንዲያውም እንዲቀለበስ ያደርጋል (ለምሳሌ ምርጫ ተጀምሮ እንደሆነ ወደ ፍፁም አምባገነንነት እንዲገባ...ወዘተ) የሚሉ ናቸው::

የአሜሪካን መንግስት ይህን መከራከሪያ የሚያቀርበው በእርግጥም ሙሉ ለሙሉ አምኖበት ነው ማለት አይደለም:: እርምጃ የማይወስደው ከራሱ የአገር ጥቅም ስሌት በመነሳት ሊሆን ይችላል:: ይህ ግን ዋናው ነጥብ አይደለም:: ዋናው ነጥብ በምንም ምክንያት ይሁን በምን እንዲህ አይነት የግፍ ወንጀል

purposive action to improve some feature of the political, social, or economic order only serves to exacerbate the condition one wishes to remedy. The *futility* thesis holds that attempts at social transformation will be unavailing, that they will simply fail to "make a dent." Finally, the *jeopardy* thesis argues that the cost of the proposed change or reform is too high as it endangers some previous, precious accomplishment." P.7.

[4] Semantha Power: "A Problem from Hell: America and the Age of Genocide."

ሲፈፀም ዝም ብሎ ማየትና ይህንንም የተለያየ የማወናበጃ ምክንያት በመደርደር ተደብቆ አላየሁም ማለት ከሞራል ተጠያቂነት አያድንም፡፡ ለዚህ ነው ክሊንተን ሩዋንዳ ድረስ ሄዶ በእልቂቱ ጊዜ ምንም ሳናደርግ ዝም ብለን በማየታችን በአሜሪካ ህዝብ ስም ይቅርታ እንጠይቃለን ያለው፡፡ ይህ እንግዲህ የሌላ አገርን ግፍ ለማስቆም ምንም ባለማድረግ ነው፡፡

በገዛ አገሩ ተቀምጦ ግፍ ሲፈፀም እራስን ቀብሮ ዝም ማለት፣ ከሰውልጅነትም በላይ በዜግነት የሞራል ግዴታን ባለመወጣት ማስጠየቁ የሚያከራክረን ሊሆን አይገባም፡፡ ይህን የሚያደርጉትም ሰዎችም ህሊና ካላቸው የሚያውቁት ይመስለኛል፡፡ ለዚህ ይመስለኛል ቶሎ ብለው በትግሉ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ለመተቸት የሚቸኩሉት፡፡ ይህ ግን በትግሉ ውስጥ ያሉት ሰዎች ጥፋት ሲያጠፉ ተቃውሞ ሊቀርብባቸው አይገባም ለማለት አይደለም፡፡ የሞራል ውሳኔ ለመስጠት አንቸኩል ለማለት ነው፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የሚፈረጁት ይህን የሞራል እኩልነት ጉዳይ ከግብዝነት ሳይሆን ከብስጭት፣ ከእልህና ከተስፋ መቁረጥ በመነሳት የሚያቀርቡትን በሚመለከት አንድ ሁለት ነገር ብዬ ልጨርስ፡፡ ምክንያቱ ምንም ሆነ ምን ከላይ ባቀረብኩት መከራከሪያ መሰረት የሞራል እኩልነት ክሱ ውሀ የሚቋጥር አይደለም፡፡ የቀረቡት «የሞራል እኩልነት» መከራከሪያዎች መሰረት የላቸውም ማለት ግን በተለይ ልባቸው ከእውነት ጋር ያለውን ግን በተስፋ መቁረጥ ምክንያት እንዲህ አይነት አስተሳሰብ ውስጥ የገቡትን ከገቡበት ጨለምተኝነት እንዲወጡ መሞከር የለብንም ማለት አይደለም፡፡ በተለይ የገጠመን የክፋት አደጋ (evil) ውጤቱ ግዙፍ በመሆኑና እሱንም ለማሸነፍ ሁሉንም ቅን አሳቢዎች ማሰባሰብ ስለሚያስፈልገው፣ ማህበረሰቡ ከገባበት ጨለምተኝነት ለማውጣት ወደ ድል የሚወስድ መንገድ መቀየስና ይህንንም ብዙሀኑን ለማሳመን መጣር አሳምኖም ለትግሉ እንዲሰለፍ ማድረግ የግድ ያስፈልገናል፡፡ ይህን ለማሳካት ደግሞ የተስፋ መቁረጡን ምክንያቶች ጠንቅቀን ማወቅ ይገባናል፡፡ እኔ እስከሚገባኝ ድረስ በኢትዮጵያ ሁኔታ የዚህ ጨለምተኝነት ምክንያቶች፡

ሀ) ኢህአዴግ የምርጫ መንገዱን በሙሉ በፍፁም መዝጋቱና በዚያ ሂደት ለውጥ ይመጣል የሚለው ግምት ከሞላ ጎደል መክሰሙ፡፡ ከዚያም በተጨማሪ ደግሞ ሌሎችን ሰላማዊ የትግል ስልቶች ለመጠቀም የሚያስፈልገው ድርጅታዊ መዋቅር አለመኖሩ ብቻ ሳይሆን ኢህአዴግ በያዘው አካሄድ ይህ መንገድ የሚያስወጣው ወጪ ቀላል እንዳልሆነ መታመኑ፣

ለ) የኢህአዴግ መንግስት ከተንገዳገደበት የ97 ምርጫ አገግሞ ምንም የማይነቃነቅ ጠንካራ መንግስት ለመምሰል የሚያደርገው ሙከራ የተወሰነውን የህብረተሰብ ክፍል ያማለለ መምሰሉ፡

ሐ) ተቃዋሚዎች የጋራ ትግል ለማድረግ የሚያስችልና ኢህአዴግን ለማስወገድ የሚችል ህብረትና ከዚያ ጋር አብሮ የሚሄድ ግልፅ የትግል እስትራቴጂና ስልት መቀየስ አለመቻላቸው፣ ይልቁንም በረባ ባልረባው እርስ በእርስ ሲናቆሩ መታየታቸው፣

መ) የአለም አቀፍ ማህበረሰቡ ለኢትዮጵያውያን ችግርና ሰቆቃ ምንም ደንታ የሚሰጥ አለመምሰሉ፣

ሰ) በተለይ በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን የዴሞክራሲ ፍላጎታቸውን እራሳቸው በሚወዱዋቸው ድርጅቶች ስር ብቻ በመከለላቸው በሰፊው ለሚደረግ የዴሞክራሲ ትግል ጥረት ሊያደርጉ የሚችሉት አስተዋፅኦ በጣም በመገደቡና የመሳሰሉት ናቸው::

እነኝህ ሁሉ ችግሮች ግን የተወሰነ እውነት ይኑራቸው እንጂ ልንወጣቸው የማንችላቸው እንቅፋቶች አይደሉም:: እንዲያውም ከላይ የተጠቀሱትን ነገሮች በደንብ ከመረመርናቸው የኢህአዴግ ጥንካሬ በግልቡ እንደሚታየው ያንን ያክል የሚፎከርበት አይደለም:: «እውነትን የያዘ ያሸንፋል» ከሚል አጠቃላይ መፈክራዊ እውነታ በመነሳት ብቻ ሳይሆን ዘርዘር ብሎ አገሪቱ ውስጥ ያለውን ሁኔታ፤ ለምሳሌ በኢኮኖማው ችግር ቅጥ ማጣት፤ ኢህአዴግ በፍፁም ካገለለውና ካበሳጨው ሰፊ የህብረተሰብ ክፍል አንፃር፤ በኢህአዴግ «ፀብ የለሽ በዳቦ» አካሄድ ምክንያት የገባባቸው ብዙ ወታደራዊ ጀብደኝነቶች በራሱ በወታደሩ ላይ እየፈጠረ ያለው የመጠቃት ስሜት፤ ኢህአዴግ እራሱ ለረጅም ጊዜ ስልጣን ላይ በመቆየቱ ምክንያት በአካባቢው በሰበሰባቸው ጉቦኞች ብዛትና ይህም የፈጠረው ቅጥ ያጣ የአስተዳደር በደል...ወዘተ የተነሳ ይህ መንግስት ከሚገመተው በላይ በጣም የተዳከመ መንግስት ነው:: ጊዜያዊ የውጭ ድጋፉም የመነጨው አመርቂ የሆነ አማራጭ በመጥፋቱ እንጂ ይህ መንግስት በአካባቢው የአለመረጋጋት ምንጭ መሆኑ ጠፍቶአቸው አይደለም::

ሌሎቹ ጉዳዮች በእኛ እጅ ናቸው:: በምንም አይነት ተስፋ የሚያስቆርጥ ሁኔታ አይደለም አሁን ሊኖር የሚገባው:: ይልቁንም አጠንክሮና አጥርቶ ማሰብ፤ በዚያ ሀሳብ ላይ ተመርኩዞ አጠንክሮ መታገል ነው የሚያስፈልገው:: ከዚህ አንፃር ለቀሪው ውይይታችን እንዲሆን በእኔ እምነት እንዴት መሄድ እንዳለብን አንዳንድ ሀሳቦችን በማጠቃለያ መልክ ልወርውር:: እነኝህ የማነሳቸው ነጥቦች ወደፊት በሰፊው ከነመከራከሪያቸው የሚተነተኑ ሆኖ ለአሁኑ ግን ዝም ብዬ ነጥብ ነጥቦቹን ብቻ ላስቀምጥ:

## 4) እንዴት ወደፊት እንሄዳለን? እንዴት በአጭር ጊዜ ለውጥ እናመጣለን?

ሀ) **ትግሉን በሚመለከት የሚያስፈልገው የአስተሳሰብ ለውጥ**: ይህ ትግል አንድን ድርጅት ወይንም አንድን የምንወደውን ግለሰብ ከስልጣን የማውጣት ትግል አይደለም፤ ሌሎች አገሮች ባለፉት 300 አመታት ታግለው ያረጋገጡዋቸውን መሰረታዊ የሆኑ የዜግነት መብቶችን (በሰብአዊ፤ በፖለቲካና በማህበራዊ) የማግኘት: እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ስርአት የመፍጠር ትግል መሆኑን ያለምንም ብዥታ መረዳት፤

ለ) ከዚህ እውነት በመነሳት ለእነኝህ መብቶች ተግባራዊነት እንቅፋት የሆኑትን ሀይሎች ማንነትና ምንነት፤ ጥንካሬያቸውንም ሆነ ድክመታቸውን እውነተኛ በሆነ (realistic assessment) ትነተና ማሳየት፤

ሐ) በዚህ ትንተና ላይ የተመሰረተ የእስትራቴጂና የስልት ውይይት ቀጥሎም ክለሳ ማድረግ፤

መ) በዚህ አመለካከት፤ እስትራቴጂና ስልት ላይ በመነሳት ለእውነተኛ ዴሞክራሲ የቆሙ ሀይሎች በሙሉ ተሰባስበው ትግላቸውን በጋራ የሚያካሂዱበት ስፊ የሆነ «አገር የማዳን የትብብር መድረክ» መፍጠርና ለዴሞክራሲያዊ ትግሉ ወጥ የሆነ የጋራ አመራር መስጠት፤

ሰ) ለዴሞክራሲ የቆሙ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ለተናጠል ድርጅት ያላቸውን ወገንተኛ ነት ወደፊት ያ ስርአት ተመስርቶ ምርጫ በሚደረግበት ጊዜ በሙሉ ልባቸው እንደሚሰጡ አውቀው፤ አሁን ግን ያንን ስርአት ለመመስረት በሚደረገው ትግል ወቅት የጋራ ትግሉን መደገፍ ብቻ ሳይሆን የጋራ ትግሉ ሊገጥሙት ከሚችሉት የመከፋፈል አደጋዎች መጠበቅንና ዴሞክራሲያዊ መስመሩን እንዳይስት መከላከልን ቅድሚያ ሰጥተው እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ ናቸው።

**ይህ ይቻላል?**

**<u>አዎን በጣም ይቻላል</u>**። ሁላችንም ከስህተቶቻችን መማር እስከቻልን ድረስ፤ በተለይ የአገር አንድነትን፤ የግለሰብንም ሆነ የቡድን መብቶችን በማክበር በኩል የጠራ አቋዋም ካለን፤ በዴሞክራሲ ጥያቄ ላይ ምንም ብዥታ ከሌለን፤ የተጠናወተንን ጠንካራ ድርጅታዊ ወገንተኝነት ትንሽም ቢሆን መቀነስ ከቻልን፤ በረጅሙ ማሰብ ከቻልን፤ እንወጣዋለን። ሁልጊዜም ከጊዜያዊ የፖለቲካ ስሌት ባሻገር ማየት መቻል ነው የሚከብደን። ይህ ትግል ስለአሁን ብቻ አይደለም፤ በአብዛኛው ስለወደፊቱ ነው። ኢህአዴግን ስለመጣል ብቻ ሳይሆን ከዚያ በሁዋላ ስለሚኖረው የተረጋጋ ማህበረሰብ በጥሞና ካሰብን ይህንን አካሄድ ከምር መውሰድ አለብን። ይህን ካደረግን ደግሞ ማሸነፋችን እርግጠኛ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ዘላቂም ድል ነው የሚሆነው።

አመሰግናለሁ።